ዘካ ለሁለት ይከፈላል:-

1. ናፊላህ(ሱና የሆነ):-
የአላህ ፊት ተፈልጎበት የሚሰጥ ሶደቃ

2. ግዴታ የሆነ:-
እሷም ደግሞ ለሁለት ትከፈላለች

ዘካቱል በደን(ዘካተል ፊጥር) :-

ዘካተል ፊጥር በትልቅ በትንሽ ፣ በወንድ በሴት ፣ በባርያ በጨዋ በአጠቃላይ በሁሉም ሙስሊም ላይ ግዴታ ነች

የገንዘብ ዘካህ:-

ዘካህ ሸሪዓ ባስቀመጠው ተመን(ሂሳብ) መሰረት ከሀብታሞች ተወስዳ ለድሆች የምትሰጥ የኢስላም ሶስተኛዋ ማእዘን(ሩክን) ስትሆን እሷም ደግሞ ወደ አራት ትከፈላለች:-

1. የወርቅ እና የብር ዘካ



ኒሷባቸው ደግሞ ለወርቅ 85ግራም ሲሆን ለብር ደግሞ 595ግራም ነው። አንድ ሰው ከነዚህ አንዱ ከደረሰ ወይንም ይህንን ያህል ግራም የሚያስገዛ ብር ካለው ዘካ ይወጅበበታል ማለት ነው።

2. የእንስሳት ዘካ



አንድ ሰው ያለው የእንስሳት ቁጥር ሸሪዓው ለዘካ ያስቀመጠው ልክ ላይ ከደረሰ ዘካ ይወጅበበታል። ዘካ የሚወጣባቸው እንስሳቶች:- ግመል ፣ ከብት ፣ ፍየል እና በግ ናቸው።

3. ከመሬት የሚበቅሉ ነገራቶች



ዘካ እነሱም:- አዝርእት እና የፍራፍሬ ናቸው።

4. ለግብይት



(ለሽያጭ የተዘጋጁ ነገራቶች)

ዘካ የሚሰጣቸው ሰዎች:-

1. ድሆች:- ምንም ለሌላቸው ድሆች ወይንም ያላቸው ነገር የማያብቃቃቸው ለሆኑ ድሆች

2. ሚስኪኖች:- ከድሆች ትንሽ ሻል ያሉ ነገር ግን ያላቸው ገንዘብ ጉዳዮቻቸውን ለማስፈፀም የማይሞላላቸው ደሀዎች

3. ለዘካ ሰራተኞች:- የዘካ ሰራተኞች ስንል የሚፈለግበት ሰብሳቢዎቿ፣ ጠባቂዎቿ እና አከፋፋይ ወኪሎቿ ናቸው። የዘካ ሰራተኞች ዘካ ለመቀበል የግድ ድሀ ካልሆኑ አይባልም ሀብታም ቢሆኑ እንኳን ሰራተኛ እስከሆኑ ድረስ ዘካ ይሰጣቸዋል። የሚሾማቸውም የሀገሩ አስተዳዳሪ መንግስት ነው።

4. ልባቸው (ከኢስላም) የሚላመድ:- ይሰልማሉ ተብለው ተስፋ የሚጣልባቸው ወይንም ከሸራቸው ለመገላገል(ለመጠበቅ) እና የመሳሰሉት ናቸው።

5. ሪቃብ (ለጫንቃ ባለቤቶች) እነሱም:-
ሀ, ከባርነት ነፃ ለመሆን የተዋዋለ
ለ, ሙስሊም ባርያን ነፃ ለማውጣት
ሐ, ሙስሊም ምርኮኛ

6. ባለ እዳዎች:-
እነሱም:-
ሀ በሰዎች መካከል ለማስታረቅ እዳ የገባ
ለ, እዳ ያለበት ሰው

7. በአላህ መንገድ ላይ ለሚታገሉ:- ለነሱ ቀለብ እንዲሆናቸው ወይንም ለትጥቅ መግዣ ይሰጣቸዋል።

8. ለመንገደኛ:- መንገድ ላይ ስንቁ ያለቀበት ሃገሩ የሚያደርሰውን ያክል ይሰጠዋል።